# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 149 መጋቢት 15 2003 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

**የትግራይ ጉጅሌ ላለፉት ሃያ አመታት በአገር እና በወገን ላይ የፈጸመው ወንጀል አልበቃ ብሎት የአገዛዝ ዘመኑን ለሌላ አስርተ አመታት ለማራዘም ደፋ ቀና የሚለው ይህ የጎጠኞችና ዘረኞች ስብስብ፤ ህዝባችን እንደሰሜን አፍሪካ ወንድሞቹ ሆ ብሎ መነሳቱ እንደማይቀር በመረዳት የለውጥ ፍላጎት ለማፈን ያስችለኛል ብሎ የሚያስባቸውን እርምጃዎች በተከታታይ እየወሰደ መሆኑን በርካታ ተግባሮቹ አመልካቾች ናቸው።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የመከላኪያ ባጀት እንደሚጨምር አስታወቀ

በሰሜን አፍሪካ ፈንድቶ አድማሱን እያሰፋ የመጣው ህዝባዊ አብዮት እረፍት የነሳው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የመከላኪያ ባጀት ለማሳደግ እንደወሰነ ባለፈው ቅዳሜ አስታወቀ።

መለስ ዜናዊ ይህንን ያስታወቀው ኤርትራንና በኤርትራ ይደገፋሉ በማለት ዘወትር የሚከሳቸው ሃይሎች የአገሪቱን ልማትና ሰላም ለማደናቀፍ ይንቀሳቀሳሉ ፤ የሰሜን አፍሪካው አይነት አብዮት ለመቀስቅስ ዕቅድ አላቸው በማለት ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጠ አንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ መሆኑ ታውቋል። “በህገመንግሥታችን መሠረት የሥልጣን ሽግግር በሰላማዊ ምርጫ ሥርዓት ሊከናወን ይችላልና ለፖለቲካ ሥልጣን አመጽ የሚያስፈልግበት ምክንያት የለም” የሚለው የትግራይ ጉጂሌ ቁንጮ ፤ “በምርጫ ሥልጣን ላይ ከወጣን ገና 10 ወር ያልሞላን ስለሆነ ስልጣን ልቀቁ ብሎ ህዝብ እንደቱኒዚያና ግብጽ አደባባይ ሊወጣብን የሚችልበት ምክንያት ሊኖር አይችልም” በማለት የ20 ዓመት የሥልጣን ቆይታ ጉዳይ እንዳይነሳ ሲሽማቀቅ ተስተውሎአል።

የአገሪቱን ሃብት ለመዝረፍ እንዲቻል በመለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ የተዘረጋው ዘረኛ መዋቅር ውስጥ የተመደቡት የአንድ አካባቢ ተወላጆች በአንድ ጀንበር ሚሊዮነሮች በሆኑበት አገራችን ቁጥራቸው እስከ 14 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎቻችን በየአመቱ ከ400 ሺ ሜትሪክ ቶን በላይ የምግብ ዕርዳታ ከውጪ እየተለገሰላቸው እንደሚኖሩ እየታወቀ የአገዛዙን ዕድሜ ለማስራዘም ሲባል ብቻ የመከላከያ ባጄት ለማሳደግ መወሰኑ የሰሜን አፍሪካው አብዮት በወያኔ ካምፕ የፈጠረው የስነ ልቦና መረበሽ ምልክት እንደሆነ ለአገዛዙ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ይናገራሉ። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ጀርመን ለኢትዮጵያ ያምታደርገውን ርዳታ እንድታጤን የጀርመን ፓርላማ ምክር ቤት ጠየቁ

ሚስተር ቲሎ ሆፐ በእንደራሴነት የሚመሩት ፅ/ቤት መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓም ባወጣው የፕሬስ መግለጫ "የዴሞክራሲን እጦትና የሰብዓዊ መብቶችን መረገጥ ክእንግዲህ ለማስተናገድ የማይሹ ድምፆች ይበልጥ እያስተጋቡ የሄዱት በዐረቡ ዓለም ብቻ አይደለም፤ ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያም እየተከሰተ ነው፡፡" በማለት መናገራቸውን የጀርመን ሬዲዮ ዶቼቨለ አማርኛው ክፍል ባወጣው ዘገባ ገለጸ።

ቀደም ብሎ በጀርመን የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ሚኒስትር ሚስተር ዲርክ ኒበል የተመራ አንድ የጀርመን መንግሥት ልዑካን ቡድን በኢትዮጵያ የሥራ ጉብኝት አድርጎ መመለሱ የገለጸው ዶቼቨለ የልኡካን ቡድኑን ጉብኝት ተከትሎ የሃገሪቱ ፓርላማ የእርዳታና የኢኮኖሚ ትብብር ኮሚቴ በዚያው ሣምንት ውስጥ በርሊን ላይ ገለፃዎችን ማዳመጡንና ከገለፃዎቹ በኋላም ተከታይ የውይይት ምሽት ማካሄዱን አውስቶ የጀርመኑ ቡንደስታግ (ፓርላማ) አባልና የእርዳታና የኢኮኖሚ ትብብር ኮሚቴው ምክትል ሊቀመንበር ሚስተር ቲሎ ሆፐ ወደ ኢትዮጵያ ተጉዞ የነበረው የጀርመን መንግሥት ልዑካን ቡድን አባል ሆነው ሄደው እንደነበር ገልጹአል፡፡ ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በኢትዮጵያ የትብብር ትግል ጥያቄ ከዚህ በፊት ከነበረው አንድ እርምጃ መሄዱን ገለጹ

ባለፉት ጊዜያት በኢትዮጵያ ሲነሳ የነበረው የትብብር ትግል ጥያቄ ከዚህ በፊት ከነበረው አንድ እርምጃ ወደፊት መሄዱን የግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃንትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ገለጹ። ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን የገለጹት ባለፈው ቅዳሜ መጋቢት 10 ቀን 2003 ዓ/ም በጀርመን ሮሰልስሃይም-ፍራንክፈርት ከተማ ተገኝተው ከኢትዮጵያውያን ጋር በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ባደረጉት ውይይት ወቅት መሆኑን ዘጋቢያችን ከፍራንክፈርት ባስተላለፈው ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል።

ዶ/ር ብርሃኑ ከጀርመን አገርና አካባቢው ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጋር ከአራት ሰዓት በላይ ውይይት ያደረጉ ሲሆን፤ ለውይይት መነሻ ያቀረቡት ጽሁፍ “የተባበረ ትግል፣የማንነት ፖለቲካ እና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ“ የሚል እንደሆነ ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል። ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን ርዕስ ለውይይቱ መነሻነት የመረጡበት ዋናው ምክንያት፤ በቅርቡ “ኦነግ“ በመሃሉ ያለውን ልዮነት ፈትቶ መምጣቱ የትብብር ትግል ለማድረግ የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው (ፎርማል) ውይይቶች ሊጀመሩ ስለሚችሉ እና እነዚህ ውይይቶች ይዘዋቸው የሚነሱ በርካታ ጉዳዮች ስለሚኖሩ፤ ማኅበረሰባችን በነዚህ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንድነት ግምባር 49 የወያኔ ወታደሮችን መግደሉን አስታወቀ

የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንድነት ግምባር በመባል የሚታወቀውና ጸረ ወያኔ ትግል ከሚያካሂዱ ቡድኖች አንዱ የሆነው ልዩ ሃይል በወሰደው የማጥቃት ርምጃ 49 የሚሆኑ የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ወታደሮችን መግደሉን አስታውቁአል። ግምባሩ በዘረኛው አገዛዝ ወታደሮች ላይ ይህን ርምጃ የወሰደው በአፋር ክልል ውስጥ ጠሩ ከሚባል የወያኔ የወታደር ካምፕ ላይ ባደረሰው ጥቃት መሆኑን መጋቢት 14 ቀን 2003 ዓም ባወጣው ወታደራዊ መግለጫ ገልጹአል። እንደ ወታደራዊ መግለጫው ፤ ጀግናው የአፍር አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር አማጽያን ከገደሉዋቸው ወታደሮች በተጨማሪ ከሃያ በላይ የሚሆኑ ከባድ የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው አስታውቆአል። የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንድነት ግምባር በዚሁ ቦታ አድርሶት በነበረው ጥቃት በርካታ የጦር መሳሪያዎችንና ቁሳቁሶችንም እንደማረከ ገልጾአል።

እንደ ወታደራዊ መግለጫው የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንድነት ግምባር በወሰደው ድንገተኛ የማጥቃት ርምጃ የዘረኛው ወያኔ ወታደሮች ከፍተኛ ድንጋጤና መሸበር ውስጥ መግባታቸውን ገልጾ በዚህ የተበሳጩ የአገዛዙ ጆሮ ጠቢ ወታደሮች በአካባቢው የሚገኙ በራካታ አርሶ አደሮችን ሰብስበው ማሰራቸውን፤ በጅምላ ከታሳሩት ሰባቱን መግደላቸውን፤ የበርካታ ሰላማዊ ዜጎች መኖሪያ ቤቶች ማቃጠላቸውንና በዙዎችን ማዋከባቸው ታውቆአል።

የግንባሩ መግለጫ በመጨረሻም ዘረኛውን የወያኔ አገዛዝ ከዚህም በላይ ጥቃት ሊፈጽምበት እንደሚችልና በጀመረውም ትግል ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አሳውቆ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔ አገዛዝ ለመጣል በሚደረገው ትግል ከጎኑ እንዲሰለፍ ጥሪውን አቅርቦአል።

## ዶር ብርሃኑ ነጋ ለአምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ርዳታ እንዳይሰጥ ለጀርመን ፓርላማ ጥያቄ አቀረቡ

ዶር ብርሃኑ ነጋ መጋቢት 10 ቀን 2003 ዓም በርሊን ውስጥ በጀርመን ፓርላማ ጉባኤ ላይ ተገኝተው ጀርመንም ሆነች ሌሎች ለኢትዮጵያ እድገትና ልማት እገዛ እናደርጋለን የሚሉ ሃገራት ለአስቸኩአይ ችግር ማስታገሻ ከሆነው የሰብአዊ ርዳታ በስተቀር ለአምባገነኑ የትግራይ ገዢ ጉጂሌ አገዛዝ ምንም አይነት ርዳታ እንዳይሰጡ አሳስበዋል። በዚሁ ጉባኤ ጀርመን በልማት ዕርዳታ ስም ላለፉት ሃያ አመታት በተከታታይ ለወያኔው ዘረኛ አምባገነን ስትሰጥ የነበረው ዕርዳታ መቀጠል ይገባዋል ወይስ አይገባውም በሚል ከፍተኛ የሆነ ክርክር ተደርጉአል፡፡

ዶር ብርሃኑ ነጋ በእለቱ ለስብሰባው ተሳታፊዎች ባደረጉት ንግግር በኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ለማምጣት የሚደረገው ትግል ሃላፊነቱ የኢትዮጵያዊያን እንደሆነና ይህም ያለምንም ጥርጥር እንደሚሳካ የገለጹ ሲሆን፣ በአንድ መልክ ወይም በሌላ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ኢትዮጵያ ውስጥ መምጣቱ የማይቀር እንደሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል በማለት ጭቆናና ግፍ የበዛበት የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድነት ተነስቶ ነጻነቱን የሚቀዳጅበት ቀን ሩቅ እንደማይሆን አስታውቀዋል። ለምራባዊያን ለጋሽ ሃገራትም ባስተላለፉት መልእክት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ መውደቁ የማይቀር መሆኑ ተረድተው ኢትዮጵያዊያን ለነጻነታቸው ሲሉ ለመክፈል የተዘጋጁት መስዋዕትነት የከፋ እንዳይሆንና ለአካባቢውም መረጋጋት አስተዋጾ እንዲኖረው ያለምንም ቅድሜ ሁኔታ በማን አለብኝነት የሚለግሱት ገንዘብ በሚሰጣቸው ጉልበት በመጠቀም መለስ ዜናዊ ከያዘው የእብደት ጉዞ እንዲቀይርና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የሚመጣበትን ነገር እንዲያስብ በጊዜ ሊነግሩት ይገባል ብለዋል። መራባዊያን ለጋሽ ሃገራቱ ይህን ማድረግ ከቻሉና ማድረግም ከፈለጉ ተግባራዊ ርምጃ መውሰጂያ ጊዜው አሁን ነውና ይህን እድል ተጠቀሙበት፣ ብለዋል፡፡ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የኦሮሞ ህዝቦች ነጻነት ግምባር (ኦ ነ ግ) ሁለት ቡድኖች እርቅ በማድረግ ተዋሃዱ

ቀደም ብሎ በመካከላቸው በተፈጠረ አለመግባባት ለሁለት ተከፍለው የነበሩት የኦሮሞ ነጻነት ግምባር (ኦነግ) ቡድኖች እርቅ ማድረጋቸውንና መዋሃዳቸውን በጋራ ባወጡት መግለጫ ላይ አስታውቀዋል። እነኝህ ሁለት ቡድኖች የእርቅ ሂደቱን የጀመሩት ከረጂም ጊዚያት በፊት እንደነበረና ልዩነታቸውንም አስወግደው ወደ አንድነት ለመምጣት እንደፈረንጆች አቆጣጠር ሴፕቴምበር 27 ቀን 2010 ላይ ተፈራርመው እንደነበር ገልጻው የዚህን ፊርማ ስምምነት ተከትሎ እንደፈረንጆች አቆጣጠር በያዝነው ወር ከሚያዚያ 29 እስከ መጋቢት 2 ቀን 2003 ዓም ባደረጉት ስብሰባ የእርቅ ሂደቱ በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁንና ሁለቱ ቡድኖች ዛሬ አንድ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በሁለቱ ወገኖች መካከል ላለፉት ሶስት አመታት የነበረው መከፋፈል የኦሮሞ ነጻነት ግምባር የነበረውን የሰው ሃይልና ማቴሪያል በመከፋፈሉ የግንባሩን ጥንካሬ ጎድቶታል ያለው ይህ የኦነግ መግለጫ የሁለቱ ቡድኖች ወደ አንድ አቅጣጫ መምጣት ኢትዮጵያዊያንን በዘር በሃይማኖትና በፖለቲካዊ ከፋፍሎ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም የሚተጋውን የዘረኛው አምባገነን ወያኔ ስራት ውድቀት ለማፋጠን ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል ብሉአል፡፡ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የትግራይ ገዢ ጉጅሌ በኦሮሞ ተወላጅ ወንድሞቻችን ላይ የከፈተውን አዲስ የእስር ዘመቻ በጽኑ እናወግዛለን!!!

የትግራይ ገዢ ጉጅሌ በቱኒዚያ ፈንድቶ የሰሜን አፍሪካንና መካለኛው ምስራቅ አምባገነኖችን እያናወጠ ባለው የለውጥ ማዕበል ክፉኛ በመረበሹ በተስፋ መቁረጥ ስሜት በወገኖቻችን ላይ እያደረሰ ያለውን ሰቆቃ አፋፍሞ ቀጥሎበታል።

ላለፉት ሃያ አመታት በአገር እና በወገን ላይ የፈጸመው ወንጀል አልበቃ ብሎት የአገዛዝ ዘመኑን ለሌላ አስርተ አመታት ለማራዘም ደፋ ቀና የሚለው ይህ የጎጠኞችና ዘረኞች ስብስብ፤ ህዝባችን እንደሰሜን አፍሪካ ወንድሞቹ ሆ ብሎ መነሳቱ እንደማይቀር በመረዳት የለውጥ ፍላጎት ለማፈን ያስችለኛል ብሎ የሚያስባቸውን እርምጃዎች በተከታታይ እየወሰደ መሆኑን የሚከተሉት ተግባሮቹ አመልካቾች ናቸው።

1. የተገደበ የሥልጣን ዘመን በህገመንግሥታቸው ውስጥ እንዳይኖር በማድረግ ከሁለት እና ሶስት አሥርተ አመታት በላይ ህዝባቸውን በሃይል አፍነው ሲገዙ የነበሩት የቱኒዚያና ግብጽ አምባገነኖች የተነሳባቸውን ተቃውሞ በመሸሽ በአገራቸው እና ህዝባቸው ላይ የከፋ ጉዳት ሳያደርሱ ሥልጣን የለቀቁበትን ዜና የአገሪቱ መገናኛ ብዙሃን እንዳይዘግቡ በመከልከል፤ በተጻራሪው የሞሃመድ ጋዳፊ መንግሥት በታቃዋሚዎች ላይ እየወሰደ ያለውን ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ ነጋ ጠባ እንዲዘገብ በማድረግ ህዝብን በፍርሃት ለማሸማቀቅ እያጣረ ነው፤
2. ከውጪ ወደአገር የሚተላለፉ ሬዲዮኖችና የቴሌቪዥን ስርጭቶች ህብረተሰባችን ዘንድ እንዳይደርሱ አልጀዚራንና ኢሳትን የመሳሰሉ ቴሌቪዥን ጣቢዎችን ለማወክ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ በመመደብ የሞገድ ጠለፋ ተግባር ውስጥ ተዘፍቋል፤
3. ህዝብ ይነሳብኛል ከሚል ፍርሃትና ስጋት የተነሳ በአገሪቱ ትላልቅ ከተሞች ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የአገዛዙ ታማኝ ካድሬዎችን፣ መለዮ ለባሾችን፣ ፖሊሶችንና የስለላ ሠራተኞችን አሰማርቷል፤
4. በሰላማዊ ትግል ለውጥ እናመጣለን ብለው በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችን ጨምሮ ለሥርዓቱ ታማኝ ያልሆኑትን ሁሉ በሰሜን አፍሪካው አይነት አብዮት አራማጅነት በመወንጀል መዛትና ማስፈራራት ጀምሯል፤
5. የህዝብን ትኩረት ለማስለወጥ ሲል ኤርትራን ለመውረር የፉከራና ዛቻ ቋንቋዎችን ማኸጎድጎድ ተያይዞታል፤
6. በተለያዩ የአገሪቱ ከተሞች የሚኖሩ ወጣቶችን ሲቻል በትናንሽ ጥቅማ ጥቅም መደለል አልያም ደግሞ በነውጥ ጠንሳሽነት በጅምላ እየወነጀለ ወደ እሥር ቤት መወርወር እንደ መፍትሄ እርምጃ ቆጥሮታል፤
7. የተቃዋሚ ፓርቲዎችን በመወከል በቅርቡ በወያኔ ምርጫ የተሳተፉትን ተቃዋሚዎች እና ቤተሰቦቻቸውን ማስፈራራት፤ ከሥራ ማፈናቀል እና ማሰር ጀምሯል፤
8. በራሱ አምሳል በመፍጠር ሥልጣን ላይ ለመቆናጠጥ የተጠቀመባቸውን ድርጅቶች ከፍተኛ እና ተራ አባላት በግምገማ ሥም በሙስናና የሥልጣን ብልግና እየወነጀለ በማፈናቀል በአዳዲስ ታማኞች የመተካት ሥራ እየሰራ ነው፤
9. ከሁሉም በላይ ደግሞ ህዝባዊ ተቃውሞ ይቀሰቅሱብኛል ብሎ የፈራቸውን ግለሰቦችን በሰበብ አስባቡ ከጎዳናና ከየቤታቸው እያደነ ማሠር ጀምሮአል። በቅርቡ በጋሞጎፋ ወገኖቻችን ላይ ከተወሰደው የመግደል እና የማሰር ወንጀል በተጨማሪ ቁጥራቸው በውል  የማይታወቅ የኦሮሞ ፌዴራሊስት እና የኦሮሞ ኮንግረስ ፓርቲዎች አባላት ታስረዋል፤ ከታሰሩት በቁጥር እጥፍ የሚሆኑት የደረሱበት አልታወቀም።

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ የሥልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል ህዝባችንን በመከፋፈል እርስ በርሱ የሚያባላበት  ወቅት እያበቃ ነው ብለን እናምናለን።

ዛሬ በየትኛውም ዘውጌ ማኅበረሰብ፣ ሃይማኖት ወይም ጾታ ላይ የሚፈጸመው ጥቃትና ሰቆቃ "እኔን አይመለከተኝም" ተብሎ የሚታለፍበ  ወቅት አይደለም። ስለሆነም የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ የከፈተውን ይህንን አዲስ ዘመቻ ለመመከት መላው ህዝባችን በጋራ መናሳት እና ለ20 አመታት በላዩ ላይ ተሸክሞ የኖረውን የጥቂቶች አገዛዝ ቀንበር ማንኮታኮት ይገባዋል እንላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ●

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የመከላኪያ . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

መለስ ዜናዊ የመከላኪያ ባጀት እንደሚያሳድግ ከመናገሩ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ በአገሪቱ የብሄር ተዋጾ ያለበት ሥርዓት የተቋቋመ ለማስመሰል ምክትል ጠቅላይ ሚንስቴርነትና የውጪ ጉዳይ ሚንስትርነት የተሰጠው የደቡቡ ተወላጅ ሃይለማሪያም ደሳለኝ፤ "የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ኤርትራ የኢትዮጵያን ተቃዋሚዎች እንዳትረዳ ያስቁምልን ካልሆነ በሃይላችን እናስቆማታለን" ብሎ አቤቱታ እንዲያቀርብ አስደርገውት እንደነበርና በተለመደው የወያኔ የሹመት ፎርሙላ ለሃይለማሪያም ደሳለኝ ታኮ ተደርጎ በምክትልነት የተመደበው የትግራይ ተወላጅ ብርሃኔ ገብረክርስቶስ ሌላ ዛቻ እና ማስጠንቀቂያ እንዳስተላለፈ ይታወቃል።

ባለፈው ቅዳሜ መጋቢት 10 ቀን በመከላኪያ መኮንኖች ምረቃ ሥነሥርዓት ላይ ተገኝቶ ባደረገው ንግግር "አገሪቱ ወደ ተሀድሶ በማምራት ላይ ስትሆን ጉዟችንን ለማደናቀፍ በኤርትራ የሚደገፉ ጠላቶቻችን ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንዳሉ ተገንዝበናል "ያለው መለስ ዜናዊ "አገራችንን ከጠላት ጥቃት ለመከላከልና የኢኮኖሚ ልማታችንን ለማረጋገጥ ወታደራዊ ወጪያችንን ከፍ እናደርጋለን፤ ጦሩም የህዝቡንና የአገሪቱን ደህንነት የመጠበቅ ሃላፊነቱን እንዲወጣ" ጥሪ እናደርጋለን" በማለት የመከላኪያ ጦር እንደ ቱኒዚያ፤ ግብጽና የመን ከህዝብ ጎን እንዳይቆም ተማጽኖአል።

በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን ያነጋገርናቸው የግንቦት 7 ከፍተኛ አመራር፤ ወያኔ በአገር ውስጥ መነሳቱ የማይቀረውን ህዝባዊ አመጽ ስላሰጋው የህዝቡን ትኩረት ወደሌላ አቅጣጫ ለመቀልበስ ሲል የጦሪነት ነጋሪት ይጎስማል እንጂ ኤርትራን ለመውረር አቅምም ሆነ ዝግጅት ኖሮት አይደለም። መንግሥት አልባ በሆነቺው ሱማሊያ የደርሰበትን ሽንፈት መለስና በዙሪያው ያሉት ጠንቅቀው ያውቁታል እና ብለዋል።

## ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በኢትዮጵያ የትብብር ትግል . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ጉዳዮች ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን አጽንዖት ሰጥቶ እንዲወያይበት እና እንዲያስብበት እንደሆነ ለተሰብሳቢዎቹ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃነታችንን ለማግኘት ችግር የሆነብን አንዱ እንቅፋት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተባብሮ አለመታገላቸው ነው የሚል አስተሳሰብ በመኖሩ የትብብር ትግል ጉዳይ የሚያጣላ አይደለም ያሉት ዶ/ር ብርሃኑ፤ አያይዘውም፤ ይህ ተባብራችሁ ታገሉ የሚለው ጉዳይ ከነማን ጋር ነው የምንተባበረው? ከዚህ ቀደም የተሞከሩ ትብብሮች ዘላቂ ሳይሆኑ ሲፈርሱ እያየን አሁንስ መተባበሩ ምን ፋይዳ አለው? የሚሉ ጥያቄዎችን ሊያስነሳ ይችላል። ሆኖም ይላሉ፤ ዶ/ር ብርሃኑ፤ እስከ አሁን ያልተነሱ ጥያቄዎች፣ በተለይ በማንነት ጥያቄ ዙሪያ ከተሰባሰቡ (እንደ "ኦነግ" አይነት) እና በኅብረ-ብሄራዊ አመለካከት ደረጃ ከተሰባሰቡት ጋር እንዴት አድርገው ነው ትብብር የሚፈጥሩት? በምን መሠረት ላይ ነው ትብብሩ የሚቆመው? እንዴትስ ቢሆን ነው ይህ ትብብር ዘላቂ የሚሆነው? የሚሉ ጥያቄዎች ይሰሙ እንጂ፣ ጠንከር ብሎና አምርሮ ከሃሳቡ ጋር የመታገል ነገር አልነበረም ሲሉ ገልጸዋል። ሆኖም አሁን እንዲህ ዓይነት ትብብር ለማድረግ ጊዜው እየመጣ ስለሆነ፤ በኋላ ሲፈጠር አላስፈላጊ እሰጥ-አገባ ውስጥ ከመግባት ከወዲሁ በጥንቃቄ ማሰቡ ተገቢ እንደሆነ በአፅንዖት አሳስበዋል።

ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን በማንነት እና ኅብረ-ብሄራዊ ሃይሎች የሚደረግ ትብብር ስናነሳ የእነዚህ ፖለቲካ ሃይሎች መሠረት ምን እንደሆነ ፅንሰ-ሃሳቡን መመልከቱ አግባብነት ያለው መሆኑን ጠቅሰው፤ ተሰብሳቢው ጥልቅና ግልጽ ግንዛቤ እንዲኖረው እያንዳንዱን በስፋት አብራርተዋል። በዚህም፤ አንድ ኅብረተሰብ ለምን ወደ ማንነት ፖለቲካ ውስጥ እንደሚገባ እና የዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ በማንነት ጉዳይ ላይ የተለያዩ ህዝቦችን በአንድ የጋራ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በማሰባሰብ የማንነት ፖለቲካን ከዜግነት ጋር በማስተሳሰርና የማኅበረሰቡ የፖለቲካ መሠረቱ የማንነት ፖለቲካ መሆኑ ቀርቶ ዜግነት ሊሆን እንደሚችል፣ ዜግነት ደግሞ አንድ አገር ውስጥ የሚገኝ ህዝብ ሁሉ የፖለቲካና ህግ እኩልነት ያለው ወይም ፍትህን መሠረት ያደረገ ዋና ሰንሰለት እንደሆነ ንድፈ-ሃሳብ በማንሳት አስረድተዋል።

በሌላም በኩል፤ የነዚህ የፖለቲካ ሃይሎች ትብብር ሊኖረው የሚችለው የአጭር እና የረጅም ጊዜ ጥቅሞች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ዶ/ር ብርሃኑ በሰፊው በማብራራት፤ በተለይ ይህንን ትብብር የሚያደርጉት እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ በዝርዝር በማሳየትና የእነዚህን ሃይሎች ልዩነቶች ይዞ እውነተኛ የተባበረ ሃይል እና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመስረት ይቻላል ወይ ብሎ  የሚያስብ፤ ጉዳዩ የተጠላለፈ ማኅበራዊ ችግሮች (ለምሳሌ፥ ታሪካዊ ችግሮች፣ የግንዛቤ ችግሮች፣ የፖለቲካ ችግሮች (እንደ ሃይማኖት ቀኖና ማየት)) ያሉት በመሆኑ በጥንቃቄ ሊታይ እንደሚገባ ጥቁመዋል።

በመጨረሻም፤ ዶ/ር ብርሃኑ ትብብሩ ሊሆን እንደሚችል እምነት ያላቸው መሆኑን ገልጸው፤ ትብብሩ የሚቻለው እንዴት እንደሆነ ለማመላከት ሞክረዋል። እንደእርሳችው እምነት ማኅበረሰባችን፤ የአመለካከት ግንዛቤ ውኸንብርን ማጥራት፣ የታሪክ እስረኛ መሆን ማቆም፣ መደራደር ጥሩ እንደሆነና የሽንፈት ምልክት አለመሆኑን መቀበል፣ የዲሞክራሲ ስርዓትን በአግባቡ መረዳት፣ ሌሎችን መስማት ብሎም ህመማቸውን ማዳመጥ መቻል፣ ከችርቻሮ ፖለቲካ መውጣት (በዲሞክራሲ ግንባታ ላይ በመሆናችን)፣ ሰፊ ትዕግስትና ተስፋ አለመቁረጥ እንዲሁም የትብብሩን አካሄድ ደረጃ በዝርዝር ለኅብረተሰቡ ግልጽ ማድረግ ከተቻለ የሚጠበቀውን የተባበረና ውጤታማ ትግል ማድረግ እንደሚቻል ገልጸዋል። በዋናነት አያይዘው ዲያስፖራው ምን ሊያደርግ እንደሚገባው ጠቃሚ ነው ያሉትን ማሳሰቢያ የሰጡ ሲሆን፤ በዚህ መሠረት ዲያስፖራው፤ ፖለቲካን እንደ ሃይማኖት ቀኖና ከሚያዩ አክራሪዎች ራሱን መጠበቅ፣ ለምክንያታዊ ሂደት መገዛት፣ በቅን ልቦና መወያየት፣ መጠየቅ፣ አይኑን ከጋራ ትግል ከሆነው የነፃነት ጥያቄ በፍጹም እንዳያነሳ አጽንዖት ስጥተዋል።

በስብሰባው የውይይት ወቅት በርካታ ጥያቄዎች ከታዳሚው ተነስተው በቂ ማብራሪያ የተሰጠባቸው ሲሆን፤ በአጠቃላይ ተሰብሳቢው በውይይቱ እጅግ የረካ መሆኑን ገልጿል። ስብሰባው ከነበረው የሕዝብ ብዛት እና ይዘት አንፃር እጅግ የተዋጣለት እንደነበረ ለማወቅ ተችሏል።

## የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር በ1996 ዓ.ም ባዘጋጀው ርዕይ 2020 የውይይት መድረክ የቀረበ (በዶ/ር ታደሰ ብሩ)

### ጽሁፉ የያዛቸው በርካታ ቁም ነገሮች ስላሉ በዚህ ጋዚጣ በተከታታይ ለማቅረብ ችለናል (ክፍል 2 ካለፈው ሳምንት የቀጠለ )

ልሂቃን የሚናገሩት፣ የሚደራደሩት፣ የሚፈራረሙት እንወክለዋለን በሚሉት የኅብረተሰብ ክፍልና በድርጅቶቻቸው ስም ይሁን እንጂ እንወክለዋለን በሚሉት ሕዝብ፣ በድርጅቶቻቸውና በእነርሱ በራሳቸው ውስጣዊ የግል ፍላጎቶች እንዲሁም በፍላጎቶችና በሚፈጽሙት ተግባር መካከል መጣመር እንዲኖር የግድ አይደለም:: የሚመሩት ኃይል ፍላጎት በልሂቃኑ ስታራቴጂያዊ ግብ ላይ ተጽዕኖ ቢኖረውም ልሂቃን የዕለት ተዕለት ተግባራቸዉን በሚመስላቸዉ መንገድ ለመምራት አንፃራዊ ነፃነት ከሌላቸዉ ልሂቃን መሆናቸዉ ይቀራል፤ ትግሉም በመሪ እጦት ተዳክሞ ይከስማል::

ስለ ልሂቃን ሚና ማሳየት የሕዝብን ሚና ማሳነስ የሚመስላቸው ሞልተዋል:: እኔ ይህ አስተሳሰብ ትክክል አይመስለኝም:: ልሂቃን ራሳቸው የሚወጡት ከሕዝብ ነውና የሕዝቡን ስነ-ልቦና፣ ሕልምና ርዕይ ይዘዉ መነሳታቸዉ ግድ ነዉ:: በሌላ በኩል ደግሞ «ሕዝብ መሪዎችን ይመርጣል» ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አንዳንዴ የምንዘነጋው ይመስለኛል:: አብዛኛውን ጊዜ ሕዝብ መሪዎቹን አይመርጥም፤ መሪዎች ራሳቸውን ነው የሚመርጡት:: በዲሞክራሲ ብቻ ነው ሕዝብ መሪዎቹን የመምረጥ መብት ያለው:: ሆኖም በዴሞክራሲም ቢሆን ሕዝብ የሚመርጠው «ልምራችሁ» ብለው ከተነሱ ልሂቃን መካከል መሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባል:: በዴሞክራሲም ቢሆን «ልምራችሁ» ያላለን ሰው «ምራን» ተብሎ አይመረጥም::

እርግጥ ነው ልሂቃን ከደጋፊዎቻቸው ተፅዕኖ ሙሉ በሙሉ ነፃ አይደሉም:: ተከታዬች መሪዎቻቸው የሚታገሉት ለሚወክሉት ሕዝብ ጥቅም እንደሆነና ለሕዝቡም ፍላጎቶች ተገዥ እንደሆኑ ማመን ይኖርባቸዋል:: ልሂቃንም ይህንን የሕዝብ አመኔታና እምነት ለመጠበቅ ሲሉ ተግባራቸው ገሃድ በሆነ መንገድ ከተከታዬቻቸው አጠቃላይ ስሜት እንዳይርቅ ይጥራሉ:: አለበዚያ ተከታዬቻቸው በከሃዲነት ሊያወግዟቸውና ለአንጃ መፈጠር አመቺ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል:: ለልሂቃን አስጊ ነገር ተቃዋሚ ልሂቅ (አንጃ) ከተከታዬቻቸው ውስጥ ሲወጣ ነው:: እንዲህ አይነቱ ከጉያ የወጣ ተቃዋሚ ልሂቅ የደጋፊዎችን ልብ በቀላሉ ማሸፈት ይችላል:: ስለዚህም ነው በአንጃዎች መካከል ያለው ቅራኔ እጅግ የከረረ የሚሆነው « … ወደው የጠሉት ሰዉ ምነው ሰው አይመስል?» እንዳለችው ዘፋኝ ማለት ነው::

እንግዲህ የዛሬ ንግግሬ አšሚ፣ ሆኖም ግን መልካም ስለሆኑ አራት ነገሮች ነው - ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ ልማት እና የልቃን ኅብረት::

### 3. *መንደርደርያ*

የ2020 ኢትዮጵያ ካለ ዲሞክራሲ እና ልማት ሰላምን፤ ካለ ሰላም እና ልማት ዲሞክራሲን፤ ካለ ሰላም እና ዲሞክራሲ ልማትን ባጠቃላይ ደግሞ ካለልሂቃን ኅብረት ሰላም፣ ዲሞክራሲና ልማት ማምጣት በእጅጉ ይቸግራታል ብዬ ስለማምን ፈተናዉ ቢበዛም አራቱንም በጥምረት የምናገኝበትን መንገድ መፈልግ አለብን ብዬ አምናለሁ:: ለዚህም ነው ዛሬ አራቱንም በጥምረት ላነሳቸው የደፈርኩት::

በበኩሌ ከመጀመርያው ዙር ርዕይ 2020 ውይይቶች ያገኘሁት ትልቅ ቁምነገር «ለችግሮቻችን መፍትሔ ማግኘት የምንችለው ልዩነቶቻችንን በማጥበብ አገራዊ ርዕይ ኑሮን ለጋራ ግብ በኅብረት ስንቀሳቀስ ነዉ» የሚለው ከድሮም ጀምሮ የነበረኝ ሃሳብ መጠናከሩ ነው::

ከዚህ በፊት በተደረጉ ውይይቶች በስፋት እንደተወሳው የኢትዬጵያ ልሂቃን ልዩነቶቻቸዉን ከማጥበብ ይልቅ ማስፋት ላይ ጊዜና ንብረት ያጠፋሉ::

መንግስታችንም ልዩነቶችን በማስፋት ላይ ተጠምዶ ቆይቶል:: የተማሩ ሰዎችም «የልዩነቶች መኖር ለእድገት አስፈላጊ ነው» ሲባል «ልዩነቶች እስከምን?» ሳይሉ በደፈናው የተቀበሉት ይመስላል:: እኔ በሰራሁበት አንድ መ/ቤት በነበርኩት ክፍል በአንድ ወቅት የነበርን ሰዎች በሃሳብ የምንግባባና ልዩነቶቻችንን በውይይት የምንፈታ ስለነበርን ለዓመታት ሰው ሳይከሰስና ሳይቀጣ በመቆየቱ ያልተደሰቱ አለቃችን «ይህ ክፍል ልዩነት ያንሰዋል» በማለት ልዩነትን «በጥበብ» በማስገባታቸዉ ዛሬ ያ ክፍል በንትርክና በብጥብጥ ተዳክሞ፣ መዳከሙንም መቀበል አቅቶት፣ «ከቀድሞዉ ዛሬ እšላለሁ» እያለ ሲከራከር ክፍሉ ራሱ ትንሽ ኢትዮጵያን ሆኖ ይታየኛል::

ስለገበያ ኢኮኖሚም ያለን ግንዛቤ ልዩነቶችን ከማስፋት ጋር የተቀናጀ ይመስለኛል:: ኢትዮጵያ ዉስጥ «ፉክክር /competition/ የገበያ ኢኮኖሚ ሞተር ነው» ማለት ኅብረት /cooperation/ የገበያ ኢኮኖሚ እንቅፋት ነው እንደማለት ተደርጎ የሚወሰድ ይመስላል:: ስለዚህም ይሆናል ስለውድድርና ፉክክር ማነስ ስናነሳ ስለኅብረት ማነስም አብረን ብዙ ጊዜ የማናነሳው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ስለኅብረት መናገር የሶšሊስት አስተሳሰብ ተደርጎ ይቆጠራል:: ውድድርና ኅብረት ተደጋጋፊ መሆናቸውን ማወቅ የተሳነን ይመስላል::

ስለአገር ስላምና ልማት ስናስብ ልዩነቶቻችን ላይ ሳይሆን አንድነታችን ላይ፤ የእርስ በርስ ፉክክር ላይ ሳይሆን ኅብረት ላይ ማትኮር ይኖርብናል ብዬ አምናለሁ:: ለዚህ የሚያበቃን ደግሞ «ሰፊው ሕዝብ» የሚባል የማይጨበጥ አካል ሳይሆን በተጨባጭ እየኖርን ያለነው ዜጎች እናንተና እኔ ነን:: ሕዝብ ባጠቃላይ ሳይሆን ግለሰብ የጥናታችን መነš ሊሆን ይገባዋል::

በእኔ እምነት የሀገርን ዕጣ ፋንታ በመወሰን ረገድ ግለሰቦች ወሳኝ ሚና አላቸው:: በተለይም ደግሞ በዕውቀታቸው፣ በችሎታቸው፣ በሙያቸው፣ በማዕረጋቸው፣ በክብራቸው፣ በሃብታቸው፣… ወዘተ ምክንያት የላቀ ተሰሚነት ያገኙ ግለሰቦች፤ ማለትም የልሂቃን፣ ሚና ወሳኝ ነው ብዬ አምናለሁ::

### 4. *የልሂቃን አደረጃጀት*

በኔ ግምት የአንድ አገር አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ ከሚወስኑ ነገሮች አንዱ - ምናልባትም ዋነኛዉ - በልሂቃን መካከል ያሉት ግኑኝነቶች መጥበቅ ወይም መላላት ነው:: በአንዲት አገር ያለው የልሂቃን አደረጃጀት ለዚያች አገር ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማት ወሳኝ ነው የሚል እምነት አለኝ:: አንዲት አገር የተበታተኑና እርስ በእርሳቸው የሚፃረሩ ወይም በርዕዮተ ዓለም የተሳሰሩ፣ አለያም በድርድር የተቀራረቡ ልሂቃን ያላት ልትሆን ትችላለች::

#### 4.1 የተበታተኑና እርስ በእርሳቸው የሚፃረሩ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ / Disunified National Elite/

በአንዲህ ዓይነቱ ማኅብረተሰብ ውስጥ ያሉ ተፃራሪ ልሂቃን መካከል ከፍተኛ የሆነ አለመተማመን በመኖሩ በግለሰብ ደረጃ የመገናኘትና በልዩነቶች ላይ የመነጋገር ፈቃድኝነት የለም:: በእንዲህ ዓይነቱ ማኅበረሰብ ፖለቲካ ማለት ሸር፣ ብልጠት፣ ጠልፎ መጣል፣ ገፍትሮ መወርመር ነው:: የአንዱ ድል የሌላው ውድቀት /zero – sum game/ ከመሆንም ባለፈ ተያይዞ መውደቅም /negative-sum game/ ይኖራል:: «ፖለቲካ ቆሻሻ ጨዋታ ነው» «ፖለቲካና ኮረንቲን በሩቁ ነው» የመሳሰሉ አባባሎች እንዲህ ዓይነት ልሂቃን ያሉባቸውን ሥርዓቶች ከመታዘብ የመነŒ አባባሎች ይመስሉኛል:: እያንዳንዱ ልሂቅ «ሰላም የሚገኘው ጠላትን ደምስሶ በመጨረስ ነው» ብሎ ሰለሚያምን ለሰላም የሚያደርገው ትግል ሌሎች ልሂቆችን በማጥፋት ማረጋገጥ ይፈልጋል:: ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱ ማኅበረሰብ አለመረጋጋት የሰፈነበት፤ በመሳሪያ ኃይል የታገዙ አመፆችና የመንግስት ግልበጣዎች የበዙበት ይሆናል:: በእንዲህ ዓይነት ማኅበረሰብ ውስጥ ዴሞክራሲን ማለም እንኳን ያስቸግራል፤ ሰላም አይኖርም፡ ልማትም እጅግ የተጓተተ ይሆናል:: ሌላው ክፋቱ ደግሞ በእንዲህ ዓይነት አገር ውስጥ ያሉ ልባም ሰዎች ራሳቸው ከፖለቲካ የሚያገሉ ከመሆኑም በላይ ፖለቲካን በአጠቃላይ የሚጠሉ፤ ትችቶቻቸውም በምፀት የተሞሉ ይሆናሉ:: ይህ ደግሞ የተማረው ክፍል ለማኅበረሰቡ ሊያበረክት ይገባው የነበረውን ያህል እንዳያበረክት ያደርገዋል:: ልባም ሰዎች ከፖለቲካ ጨዋታው ራሳቸውን በማግለላቸውም የመጠፋፋቱን ጨዋታ በአሸናፊነት የሚወጡት ጨካኞችና ምህረት የለሾች፤ መሰሪዎችና ቂመኞች ናቸው:: እናም ፖለቲከኛ ማለት ተንኮለኛ፣ መሰሪ፣ ቀጣፊ፣ ማለት ነው በሚል ቅንና ደግ አላሚዎች የማይመኙት ሙያ ይሆናል:: ብዙዎቹ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገሮች በተለይም ደግሞ የአፍሪካ ቀንድ አገሮች በእንዲህ ዓይነቱ ልሂቃን የተገነቡ በመሆናቸው ሰላምም፣ ዴሞክራሲም፣ ልማትም ርቀዋቸው በƒስቱ የዓለም ጭራ ሆነዋል::

#### 4.2 በርዕዮተ-ዓለም የተሳሰሩ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ /Ideologically Unified National Elite/

በአንድ ማኅበረሰብ ያሉ ልሂቃን ለአንድ ርዕዮተ ዓለም የተገዙ ሊሆኑ ይችላሉ:: ይህ ገዥ ርዕዮተ-ዓለም ለሁሉም ጥያቄዎች የማያšማ መልስ ያለው ተደርጎ ስለሚወሰድ ልሂቅነት የሚወሰነው ርዕዮተ-ዓለሙን በመረዳትና ተግባራዊ በማድረግ ብቃት ይሆናል:: ሃይማኖቶች ለዘመናት ይህን ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል:: ቆይቶ ደግሞ ሊኒኒዝም፣ ስታሊኒዝም፣ ማኦኢዝም፣ …፣ ወዘተ፣ በተመሳሳይ መንገድ አገልግለዋል:: አሁን ደግሞ በአገራችን «አብዮታዊ ዲሞክራሲ» ተመሳሳይ ሚና ለመጫወት የሚሞክር ይመስላል:: የዚህ ርዕዮተ-ዓለም /ሃይማኖት/ ዋናው ሚና ሁሉምን ዜጋ በአንድ አይነት ቅርጽ ሞርዶ ማውጣት ነው:: በርዕዮተ-ዓለም የተሳሰሩ /ideologically unified/ ልሂቃን ባሉበት ማኅበረሰብ የርዕዮተ-ዓለሙ አራማጅ መሪ ድርጅት መኖር የግድ ነው:: ከዚህ ድርጅት የተለየ ሌላ ድርጅት እንዲኖር አያስፈልግም፤ አይፈቀድምም:: የድርጅቱ መሪዎች ርዕዮተ-ዓለሙ በደንብ የገባቸውና የመተርጎም ብቃት ያላቸው ሰዎች ናቸው:: ሌሎች አውራዉ ልሁቅ ያለውን የሚደግሙ፤ ያሰበውን የሚያስቡ፣ ናቸው:: በእንዲህ ዓይነት ማኅበረሰብ ፖለቲካ ማለት መሪውን ርዕዮተ-ዓለም ማጥናት፣ ማንጠር፣ መተንተን፣ መፈትፈት፣ … «ፀጉር መሰንጠቅ»፣ ማለት ነው:: እዚህ ፖለቲከኛ ሸምዳጅ፣ ባህታዊ፣ ጥራዘ ነጠቅ እና ራሱን በማርቀቅ የሚመፃደቅ ነው:: እንዲህ አይነቱ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ የሃሳብ ልዩነቶችን ፈጽሞ የማያስተናግድ በመሆኑ ዲሞክራሲ አይታሰብም:: እንዲህ ዓይነቱ ማኅበረሰብ ሰላም የሰፈነበት ሊሆን ይችላል:: በተወሰነ መጠንም ልማት ሊኖር ይችላል:: ልማቱ ግን በነፃነት ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ ጠንካራ መሠረት አይኖረውም:: Šቲካን እንደ አገር ለማየት ካልቸገርን ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናት:: የቀድሞዋ አልባኒያና ሶቭየት ኅብረትም ተቀራራቢ ምሳሌዎች ናቸው:: ዛሬ ደግሞ ሰሜን ኮሪያ፣ ኩባ፣ ሳውድ አረቢያ፣ ሊቢያ፣ ….. እያልን መዘርዘር እንችላለን::

(ክፍል 3 ሳምንት ይቀጥላል)

## የጸጥታው ምክር ቤት ያስተላለፈው ውሳኔ ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ግምባታ የሚታገሉ ሃይሎችን የሚያበረታታ ነው ተባለ

ዓለም አቀፉ የጸጥታው ምክር ቤት መጋቢት 10 ቀን 2003 ዓም ባደረገው ስብሰባ በሊቢያ ላይ ጠንካራ ርምጃን መውሠድ የሚያስቿል ውሳኔን ያስተላለፈ ሲሆን እዚህ ውሳኔ ላይም የተደረሰው ሙሉ በሙሉና ያለምንም ተቃውሞ በተሰጠ የጸጥታው ምክር ቤት አባል ሃገራት ውሳኔ ነው።

ራሱን የነገስታት ንጉስ በማለት የሚያሞካሸው ሙአመር ጋዳፊ በሊቢያዊያን እንፈልግህም የአርባ ሁለት አመታት አገዛዝ አንገሽገሸን እናም በቃከን ከተባለ ወዲህ ራሱን ስልጣን ላይ ለማቆየት በሺሆች በሚቆጠሩ ንጹህ ሊቢያዊያንን በአየር ሃይል በምድር ሃይልና በእግረኛ ተዋጊዎች እየጨፈጨፈ መሆኑ እጂግ ያሳሰበው የጸጥታው ምክር ቤት ጋዳፊን ከዚህ ተግባሩ የሚያስቆም ፤ ሊቢያዊያን የነጻነት ታጋዮች ደግሞ ትግላቸውን አጠናከረው በመቀጠል ከጋዳፊ አገዛዝ ነጻ የሚወጡበትን እድል የሚፈጥር ጠንካራ ውሳኔ አስተላልፉአል። ምክር ቤቱ ጋዳፊ በሊቢያዊያን ላይ የሚያደርገውን ህገወጥ ጭፍጨፋ ለማስቆም ማንኛውንም ርምጃ እንደሚወስድ ያስታወቀ ሲሆን በእለቱ ፈረንሳይና ኖርዎይ ወታደራዊ ሃይላቸውን ወደሊቢያ ለመላክ ቃል ገብተዋል።

ይህን የጸጥታው ምክር ቤት ውሳኔን አስመልክቶ አስተያየታቸውን የሰጡን አንድ የፖለቲካ ተንታኝ እንደገለጹት በአሁኑ ወቅት በሰሜንና መካከለኛው ምስራቅ አፍሪቃ እየታየ ካለው ህዝባዊ አንብዮት አንጻር በሊቢያና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ተመሳሳይነት ከሌሎች የሰሜን አፍሪቃ ሃገራት አምባገነኖች የበለጠ እንደሚቀራረብ ገልጸው የጸጥታው ምክር ቤት የወሰደው ርምጃ እንደመለስ ዜናዊ ያሉ ዘረኛ አምባገነኖች በወታደራዊ ሃይል ላይ ተማምነው በህዝብ ላይ ግፍ መፈጸም እንደማይቿሉ ቆንጠጥ የሚያደርግ መለክትን ያስተላለፈ ነው ብለዋል። ቀጥለውም ኢትዮጵያዊያን በሃገራቼን ያለውን ዘረኛና አምባገነን ስርአት ከስሩ መንግለን ለመጣል አሁን ከተገኘው አጋጣሚ የተሻለ እንደማይኖር፣ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም የተጠናከረ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ለሚያደርጉ ሙሉ ድጋፉን የሚሰጥ መሆኑ የሚያጠራጥር ባለመሆኑ የተጀመረውን ህዝባዊ እንቅስቃሴአችንን አጠናክረን ለድል መቅብቃት ይኖርብናል ብለዋል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የትግራዩ ገዢ ጉጂሌ በተለይም በቱኒዚያ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመጽ ወደ በርካታ ሃገራት ከተዛመተ ወዲህ እጂግ ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ መግባቱን በዚህም ምክንያት ህዝባዊ አመጽ ይነሳብኛል በመፍራት ሰዎችን ማሰርና ማዋከብ እንደቀጠለ መሆኑን በስፋት መዘገባችን ይታወሳል።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በአውሮፓ ቤልጂየም ያካሄደው ስብሰባ በኪሳራ ተጠናቀቀ

ዘረኛውና አምባገነኑ የትግራይ ገዢ ጉጂሌ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዲያስፖራው ውስጥ በመግባት የመከፋፈል ስራውን ተግባራዊ ለማድረግ እንቅልፍ አጥቶ እየሰራ ቢሆንም በውጪ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን እየሰጡት ያለው ምላሽ አስደንጋጭ እየሆነበት መምጣቱን የግንቦት ሰባት ሪፖርተር ከቤልጂየም ባስተላለፈልን ዘገባ ለማወቅ ተችሎአል።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት አፍቃረ ህወሃት በሆኑ ሁለት የትግራይ ብሄር ተወላጆች አስተባባሪነት ባለፈው ዓርብ መጋቢት 9 ቀን 2003 በአንተወርፕ ከተማና አካባቢው ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን "ፓስፖርት ፤ የመኖሪያ ግንባታ ቦታ እና ኮንዶሚኒዬም ለማግኘት ትችሉ ዘንድ ኤምባሲው ከናንተ ጋር ለመነጋገር ይፈልጋል " በሚል ሰበብ የተጠራው ስብሰባ ላይ የተገኙት ስብሰባውን ለመምራት ከኤምባሲው የተላኩትን 3 አዳዲስ የወያኔ ሹመኞችን ጨምሮ 30 ሰዎች ብቻ ነበሩ።

በእለቱ ተደርጎ በነበረ በዚህ ስብሰባ ላይ የትግራዩ ገዢ ጉጂሌ ምእራባዊያንን ለማደናገር ስለነደፈው የትራንስፎርሜሽን እቅድ የተለመደውን አሰልቺ ፕሮፓጋንዳ መንዛቱንና አሁንም በአምስት አመት ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገራት ተርታ ለማድረስ ደፉ ቀና እያልን ነው በማለት አዳማጭ በሌለበት አዳራሽ ሰበካ ሲካሄድ መቆየቱ ታውቁአል። ይህን አሰልቺ ስብከት ለማነብነብ በኤምባሲው ውስጥ በሚንስትር ካውንስል ደረጃ የተመደበ ግለሰብ እና ሁለት አንደኛ ደረጃ ጸሃፊዎች በቦታው ተገኝተው እንደነበር ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቱአል።

በስብሰባው ላይ ከተገኙት አብዛኛዎቹ እንጀራ ፈላጊ የሆኑ እና የመኖሪያ ፈቃድ ካገኙ ቦኋላ ዘመድ አዝማድ ለመጠየቅ በሰላም አገር ቤት ገብቶ መውጣትን እንደጸጋ የሚቆጥሩ ዜጎች መሆናቸው ታውቆአል።

ይህ በዚህ እንዳለ ዘረኛውና አምባገነኑ የትግራይ ገዢ ጉጂሌ የዲያስፖራው ሃይል ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሰጋው በመምጣቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አዲስ ዘመቻ መክፈቱንና የዚሁ ዘመቻ አካል የሆነ ስብሰባ የፊታችን አፕሪል 9 እና 10 በአሜሪካን ሃገር በሚገኙ አስራ ሁለት የተለያዩ ከተሞች በአንድ ጊዜ ሊያከናውን ማቀዱን አይጋ ፎረም የተባለ የወያኔ ድህረ ገጽ አስታውቆአል። አይጋ ፎረም ለንባብ ባበቃው ማስታወቂያ እንደተዘገበው ስብሰባዎቹ የሚካሄዱት በዋሽንግተን ዲሲ፣ አትላንታ፣ ኮሎምበስ፣ ሚኒያ ፖሊስ፣ ዳላስ፣ ቦስተን፣ ዴንቨር፣ ሲያትል፣ ሎስ አንጀለስ፣ ሳንሆዝ ፤ ላስ ቬጋስና፣ ኒውዮርክ ሲሆኑ በካናዳ ደግሞ ቶሮንቶና ኦታዋ መሆናቸው ታውቁአል። ስብሰባውን ለማካሄድ ከኢትዮጵያ በርካታ የጉጂሌው አቀንቃኞች ወደ ውጪ ሃገራቱ እንደሚጉአዙም ዜናው አክሎ ገልጹአል።፡ ወያኔ በሰሜን አሜሪካ የጠራውን ይህንን ሰብስባ ለማምከንና ህዝቡን ለመስብሰብ የሚመጡትን ወንጀለኞች ለማጋለጥ ስብሰባው በሚካሄድባቸው ከተሞች እና አካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እንቅስቃሴ መጀመራቸውን በየከተሞቹ የሚገኙ የግንቦት 7 ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል።

ዘረኛው የትግራይ ገዢ ጉጂሌ በኢትዮጵያዊያን ስም የሚሰበሰብን የልማት ርዳታ እጂግ በሚሰቀጥጥ ሁኔታ እየመዘበረ እንደሚገኝና ምዝበራ ከሚካሄድባቸው መንገዶች አንዱ የአገዛዙ አሽቃባጮች ወደ ውጪ ሃገራት ሲጉአዙ የሚወጣው ወጪ እንደሆነ በተደጋጋሚ መዘገባቸን አይዘነጋም።

## ጀርመን ለኢትዮጵያ ያምታደርገውን ርዳታ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ሚስተር ቲሎ ሆፐ፤ የጀርመን ፓርላማ አባልና የፓርላማው የእርዳታና የኢኮኖሚ ትብብር ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ለዘረኛው የትግራይ ገዢ ጉጂሌ ቁንጮ ስለመሬት መቀራመት፣ በኢትዮጵያ ስለ ሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች አንስተው ጠይቀውት እንደነበር፣ መለስም ሁሉም ነገሮች ከተቃዋሚዎች የሚፈልቁ ውሸቶች ናቸው ማለቱን ገልጸው፤ እኔ ግን መለስ የነገረኝን አላመንሁትም ማለታቸው ታውቁአል።

የቡንደስታጉ የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ኮሚቴ ከኢትዮጵያ ተቃዋሚ መሪዎችና የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ጋር ተገናኝቶ መነጋገሩን የእንደራሴ ቲሎ ሆፐ ፅ/ቤት መግለጫ አመልክቶ ኮሚቴው ያነጋገራቸው የፖለቲካ ሰዎችና የመብቶች ተሟጋቾች አዲስ አበባ ውስጥ የተቃውሞ ሰልፍ ማካሄድ መከልከሉን፣ ሥርዓቱን የሚተቹ ጋዜጠኞች፣ ፖለቲከኞችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተጠሪዎች እንደሚታሠሩ ያስረዱ መሆኑን ገልጿል፡፡

የጀርመን መንግሥትም ከኢትዮጵያ ጋር ወደኢኮኖሚ ልማት ትብብር ድርድሮች ሲገባ እነዚህን አሣሣቢ ያሏቸውን የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ እንዲያስገባ የሚስተር ቲሎ ሆፐ ፅ/ቤት የፕሬስ መግለጫ ማሳሰቡን ዶቿቨለ ዘግቡአል፡፡

ቀደም ብሎ ባለፈው ሳምንት የዜና ዘገባችን የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በጀርመን ፓርላማ ተገኝተው ንግግር ማድረጋቸውን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ዘረኛ አገዛዝ መውደቁ ፍጹም አይቀሬ መሆኑን ለፓርላማ አባላቱ መናገራቸውንና የጀርመን መንግስትም ሆነ ምእራባዊያን መለስ እየተከተለ ካለው የእብደት ጉዞ እንዲያቆም ማድረግ የሚችሉበት ቀዳዳ ካለ ማድረጊያ ጊዜያቸው አሁን ነው ማለታቸውን መግለጻችን ይታወሳል፡፡

## ዶር ብርሃኑ ነጋ ለአምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በዚሁ ጉባኤ የጀርመን አረንጉዋዴው ፓርቲ ተጠሪ ሚስተር ቲል ሆፐ ባደረጉት ንግግር የጀርመን ሸንጎ የየሃገሪቱን የርዳታ ጥያቄ ከቦታ ቦታ ለይቶ ማየት ያስፈልገዋል፣ የልማትና የእድገት ርዳታ ከሰብአዊ መብቶች መከበር ጋር አብረው ተያይዘው እጂ ለእጅ የሚሄዱ ነገሮች ናቸው፣ ይህ ከሆነ ደግሞ በአንድ ሃገር ውስጥ ሰብአዊ መብቶች ሲረገጡና ሲደፈሩ ዝም ብለን አይተን አይናችንን ጨፍነን እንዳላየን ማለፍ አንችልም ካሉ በኋላ ፤ ለኢትዮጵያ መንግስት የሚደረገው የገንዘብ ርዳታ የፖለቲካ ተቃዋሚ ቡድኖችን ለመጨቆኛ እየዋለ ነው ብለዋል። በጀርመን ሃገር የሂዩማን ራይትስ ዋች ተጠሪ የሆኑት ሚስተር ወልፍጋንግ ቡትነር በበኩላቸው የኢትዮፕያው አምባገነን አገዛዝ ባለስልጣናት ከም ዕራብ ለጋሾች የሚለገሳቸውን ገንዘብ የፖለቲካ ድጋፍ ማግኛ አድርገው ይጠቀሙበታል በማለት ያላቸውን ማስረጃ አጣቅሰዋል።

በዚሁ ስብሰባ የተገኙት ዶር መረራ ጉዲና በበኩላቸው ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያ መንግስት በአሁኑ ሰአት ከመጥፎነት ወደባሰ ዝቅጠት ሙሉ በሙሉ የወረደበት ጊዜ ላይ እንገኛለን፣ በኢትዮጵያ የአንድ ፓርቲ አምባገነን ስርአት ሙሉ በሙሉ ሁሉንም ነገር ተቆጣጥሮና በኢትዮጵያ ህዝብ ትከሻ ላይ በጉልበት ተቀምጦ ይገኛል ብለዋል። አስከትለውም ገዢው ፓርቲ ተቃዋሚን በማሸመድመድ አገኘሁ በሚለው 99.6 በመቶ ህዝብ ድምጽ ቀደም ሲል ለይስሙላ በፓርላማው ውስጥ ተቃዋሚዎች የነበራቸውን ድርሻ ጠቅልሎ በመውሰድ የአንድ ፓርቲ አገዛዝ አስፍኖአል፣ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች አያያዝም ቀደም ብሎ ከነበረበት ሁኔታ በከፋ መልኩ ተረግጦ የሚገኙበት ሁኔታ ላይ ነን ብለዋል። ዶር መረራ በመጨረሻም ዛሬ በኢትዮጵያ የሚገኘው የፖለቲካ እስረኛ ቁጥር ከዚምባቡዌ በእጂጉ እንደሚበልጥ ተናግረው በዴሞክራሲያዊነት ሚዛን ሲቀመጡ የዚምባቡዌው ሮበርት ሙጋቤ ከመለስ ዜናዊ የተሻሉ ናቸው በማለት ፤ የምእራቡ ዓለም ከእንዲህ አይነት አምባገነኖች ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት እንደገና መመርመር ይገባዋል ብልዋል።

## የኦሮሞ ህዝቦች ነጻነት ግምባር (ኦ ነ ግ) . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ውህዱ የኦሮሞ ነጻነት ግምባር ለደጋፊዎቹና ለኢትዮጵያ ህዝብ ባስተላለፈው መልእክት በሰሜን አፍሪቃ የሚገኙ ሃገራት ዜጎች በየሃገሮቻቸው ያሉትን አምባገነን አገዛዞች ከጫንቃቸው ላይ አሽቀንጥረው በመጣል የህዝባዊ አብዮትን ሃያልነት ያሳዩን በመሆኑ እኛም በአንድነት ይህን ዘረኛ አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሆ ብለን እናስወግድ፣ የሰሜን አፍሪቃው ታሪክ በኢትዮጵያ ይደገም ብለዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለዲሞክራሲ የተባለው የ3 ድርጅቶች ጥምረት የኦነግ አመራር በመካከላቸው የነበረውን ልዩነት አስወግደው ወደ አንድነት መመለሳቸውን አስመልክቶ አንኳን ድስ ያላችሁ በማለት በትናንትናው ዕለት መጋቢት 9 ቀን መግለጫ አውጥቶአል። የኦነግ አመራር ድርጅታቸውን መልሶ ማዋሃድ የጸረ ወያኔ ትግሉን በማጠናከር በአገራችን ፍትህ ነጻነትና ዲሞክራሲ እንዲገነባ የሚደረገውን ትግል ያጠናክረዋል ያለው የጥምረቱ መግለጫ፡ የሰሜን አፍሪካን አምባገነኖች እያርበተበተ ያለው ህዝባዊ አብዮት ከሳሃራ በታች ወዳለቺው አገራችን እንዲዛመትና የተሳካ ለውጥ በአገራችን እንዲመጣ ኦነግ ከሌሎች የአገሪቱ ዲሞክራቲክ ሃይሎች ጋር ሆኖ ለመታገል ወቅታዊ ሃላፊነት አለበት ፤ ይህንንም ሃላፊነት ለመወጣት ተዘጋጅቶአል ብለን እናምናለን ብሎአል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org